በአንድ ነገር ውስጥ ገራገርነት (ልስላሴ) አይኖርም ያስዋበው ቢሆን እንጂ ፤ ከአንድ ነገር ውስጥ ደግሞ አይነሳም አስቀያሚ የሚያደርገው ቢሆን እንጂ።

የነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ባለቤት ከሆነችው ከእናታችን ዓኢሻህ -አላህ መልካም ስራዋን ይውደድላትና- እንደተላለፈው ነቢዩ
ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል፦ "በአንድ ነገር ውስጥ ገራገርነት (ልስላሴ) አይኖርም ያስዋበው ቢሆን እንጂ ፤ ከአንድ
ነገር ውስጥ ደግሞ አይነሳም አስቀያሚ የሚያደርገው ቢሆን እንጂ።" [ሶሒሕ ነው።] [ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በንግግርም ይሁን በተግባር ገራገርነት፣ ለስላሳነትና እርጋታ ነገሮች ላይ ውበት፣ ምሉዕነትና ማማር የሚጨምር እንዲሁም ይህንኑ ባህሪ የተላበሰ ሰውም ጉዳዩን ለማሳካት የተገባ እንደሆነ ገለፁ። ገራገር (ለስላሳ) አለመሆን ደግሞ ነገሮችን ያነውራቸዋልም አስቀያሚ ያደርጋቸዋልም፤ ስለዚህም ባለቤቱ አላማውን እንዳያገኝ ይከለክለዋል። ካገኘም በችግር ነው የሚያገኘው።

https://sunnah.global/hadeeth/am/show/5796